በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ኦርቶዶክሳዊ ወጣት

እና

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት

ወጣትነት

እግዚአብሔር ይፈልገዋል

ዓለምም ትፈልገዋለች

ለማን ይዋል?

ወጣትነት

እንደ አቶሚክ ኃይል ነው።

- የ1950 የኢትዮጵያ ወጣቶች ሁኔታ
- የ1950 የግብጽ ወጣቶች ሁኔታ

ወጣትነት በጎ ተጽእኖ

1. ዮሴፍ

“ዮሴፍም የ17 ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ ከወንድሞቹ ጋር በጎችን ይጠብቅ ነበር፣ እርሱም ከአባቱ ሚስቶች ከባላና ልጆች ጋር ሳለ ብላቴና ነበረ፤ ዮሴፍም የክፋታቸውን ወሬ ወደ አባታቸው አመጣ። እስራኤልም ዮሴፍን ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ ይወደው ነበር።”

ዘፍ. 37፡2-3

2. ሠለስቱ ደቂቅና ዳንኤል

- ናቡከደነፆርን ያስደነቀው የወጣቶቹ ጽንዓት ነበር።

“ናቡከደነፆርም መልሶ፦ መልአኩን የላከ፣ ከአምላካቸውም በቀር ማንንም አምላክ እንዳያመልኩ ለእርሱም እንዳይሰግዱ ሰውነታቸውን አሳልፈው የሰጡትን፣ የንጉሡም ቃል የተላለፉትን በእርሱ የታመኑትን ባሪያዎቹን ያዳነ፣ የሲድራቅ፣ የሚሳቅና የአብደናጎም አምላክ ይባረክ። እኔም እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ የለምና በሲድራቅ በሚሳቅና በአብደናጎ አምላክ ላይ የስድብን ነገር የሚናገር ወገንና ሕዝብ በልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ይቆረጣሉ፣ ቤቶቻቸውም የጉድፍ መጣያ ይደረጋሉ ብዬ አዝዣለሁ አለ።” ዳን. 3፡28-29

3. በጌታችን ጉባኤ የተገኘው ወጣት

“አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና በዚህ አለ።” ዮሐ. 6፡9

4. ቅዱስ አትናቴዎስ

5. ሐቢብ ጊዮርጊስ

ወጣትነት እና መጥፎ ተጽእኖ

1. ከሃዲው ጁሊያን (ዑልያኖስ) – (Julian the Apostate)

361-63 የሮማን ኢምፓየር ቄሣር

2. ቻርለስ ዳርዊን

3. ጆሴፍ ስታሊን

ከወጣቶች ምን ይጠበቃል?

1. ክርስትናን እና ቤተ ክርስቲያንን በትክክል መገንዘብ

“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።” የሐዋ. 1፡8

በኢየሩሳሌም፣

በይሁዳም ሁሉ፣

በሰማርያም፣

እስከ ምድር ዳርም ድረስ

“ሁሉም ኢየሱስ ባደረገው ሁሉ ሲደነቁ ለደቀ መዛሙርቱ፦ የሰው ልጅ በሰው እጅ ይሰጥ ዘንድ አለውና እናንተ ይህን ቃል በጆሯችሁ አኑሩ አለ። እነርሱ ግን ይህን ነገር አላስተዋሉም፣ እንዳይገባቸው ተሰውሮባቸው ነበር፤ ስለዚህም ነገር እንዳይጠይቁት ፈሩ። ከእነርሱም ማን እነዲበልጥ ክርክር ተነሣባቸው። ...” ሉቃ. 9፡44-47

2. ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ሁኔታ በትክክል መገንዘብ

- “It isn't that they can't see the solution. It is that they can't see the problem.”

G.K. Chesterton

3. ቁርጠኝነት

“የሎጥን ሚስት አስቢት” ሉቃ. 17፡32

- ያለቆረጠ ሰው የትም መድረስ አይችልም።
- “በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል።” ማቴ. 16፡24

4. ዋጋ የሚከፍል ትውልድ መሆን

- ዋጋ ለመክፈል ያልተዘጋጀ ትውልድ ውጤት ማግኘት አይችልም።
- “አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና። እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ።”
- “የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል÷ የሚዘራና የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል።” ዮሐ. 4፡36-38

ቁርጠኛ የሆኑ የኦርቶዶክሳውያን አገልጋዮች ምልክቶች

ሀ. ምክንያት ከመፈለግና ከመደርደር ይልቅ በእምነት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም ጨክነው ይሠማራሉ።

ለምሳሌ፡- አበ ብዙሃን አብርሃም ልጅህን መሥዋዕት አድርግህ አቅርብልኝ ተብሎ ሲጠየቅ ያለ ምንም ማመንታት፤ ክርክርና ተቃውሞ ይስሐቅን አቀረበው።

ቅዱሳን ሐዋርያት - ተከተሉኝ” ሲላቸው . . .

- “በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ። በሄዱ ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ።” መዝ. 126፡5-6

ለ. ውጫዊ በሆኑ ተጽእኖዎች ተጠልፈው አይወድቁም።

- - ሎጥ በሰዶምና በገሞራ ሲኖር ራሱን በዚያ ከሚኖሩት ሰዎች ነውር ጠብቆ እንደ ነበር። ዘፍ፣ 19

- - ኖኅና ቤተሰቡ ክፋት በሠለጠነበት በዚያ ጊዜ እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት እየኖሩ በደረቅ መሬት ላይ መርከብ እንደ ሠሩ። ዘፍ. 6
- ብርሃን ሆኖ ለሌሎች ሊያበራ፣ ጨው ሆኖ አልጫ የሆኑትን ሊያጣፍት እንጂ እርሱ ራሱ ሊጨልምና አልጫ ሊሆን አይገባውም።

ሐ. ራሱን በውለታ፣ በይሉኝታና በመሳሰሉ ነገሮች አያታልልም።

- “የሰዶም ንጉሥም አብራምን፦ ሰዎቹን ስጠኝ፥ ከብቱን ግን ለአንተ ውሰድ አለው። አብራምም የሰዶምን ንጉሥ አለው። ሰማይንና ምድርን ወደሚገዛ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጄን ከፍ አድርጌአለሁ። አንተ፦ አብራምን ባለጠጋ አደረግሁት እንዳትል፥ ብላቴኖቹ ከበሉት በቀር ከእኔ ጋር ከሄዱትም ድርሻ በቀር፥ ፈትልም ቢሆን የጫማ ማዘቢያም ቢሆን፥ ለአንተ ከሆነው ሁሉ እንዳልወስድ አውናን ኤስኮልም መምሬም እነርሱ ድርሻቸውን ይውሰዱ።” ዘፍ. 14፡21-24
- ሦስቱ ወጣቶች -
- ነቢዩ ዳንኤል . . .

መ. የእምነት ሰው መሆን አለበት።

- “ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።” 1 ዮሐ. 5፡4

- “ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና። ኖኅ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ስዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ፥ በዚህም ዓለምን ኰነነ፥ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።

- “አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፥ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ። እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፥ ጽድቅን አደረጉ፥ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ፥ የአንበሶችን አፍ ዘጉ፥ የእሳትን ኃይል አጠፉ፥ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፥ ከድካማቸው በረቱ፥ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፥ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ።”

ዕብ. 11

ሠ) ችግር የሚያወራ ሳይሆን መፍትሄ የሚፈልግ ነው።

- ችግር የሚያወራ የችግሩ አካል ነው፤
- ስለዚህ የችግሩ አካል ሳይሆን የመፍትሔው አካል የሚሆን ሰው ያስፈልጋል።
- “ኢየሱስም ዓይኖቹን አንሥቶ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየና ፊልጶስን። እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን? አለው። ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው ይህን ተናገረ። ፊልጶስ፦ እያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ እንኳ እንዲቀበሉ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ አይበቃቸውም ብሎ መለሰለት። ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ። አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና በዚህ አለ፤ ነገር ግን እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆናል? አለው።” ዮሐ. 6፡5-9

ስብሐት ለእግዚአብሔር